| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ካሻንጉሊት ፡ ተውኔት ፡ ተመልካችነት ፡ ወደሀገር ፡ ባለቤትነት ፡ ይሸጋገር ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2015-001 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ካሻንጉሊት ፡ ተውኔት ፡ ተመልካችነት ፡ ወደሀገር ፡ ባለቤትነት ፡ ይሸጋገር ።




« ማንትስ ፡ ታሰረ ፡ ... ፣ ማንትስ ፡ ተፈታ ፡ ... ፤ ማንትስ ፡ ከዳ ፡ ... ፣ ማንትስ ፡ ተባረረ ፡ ... ፤ ማንትስ ፡ ሰረቀ ፡ ... ፣ ማንትስ ፡ ዝምታውን ፡ ሰበረ ፡ ... ፤ ማንትስ ፡ ሸፈተ ፡ ... ፣ ማንትስ ፡ እጁን ፡ ሰጠ ፡ ... ፤ ማንትስ ፡ ተነበየ ፡ ... ፣ ማንትስ ፡ አጋለጠ / ተጋለጠ ፤ ወዘተርፈ ፡ ... » ፡ እየተባለ ፥ ላለፉት ፡ አርባና ፡ ኀምሳ ፡ ዓመታት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በግብዝ ፡ አለኝታና ፡ በከንቱ ፡ ተስፋ ፥ የትግሉን ፡ ጐራ ፡ ላስመሳዮች ፡ ለቆ ፣ በተመልካችነት ፡ አረፍቆ ፡ ኖረ ። ጠላትም ፥ ይህን ፡ የሕዝብን ፡ መዘናጋት ፡ በማየቱ ፥ ጕዳዩን ፡ የባሰውን ፡ ከመናቁ ፡ የተነሣ ፥ ኢትዮጵያዊ ፡ ዜግነት ፡ የሌላቸውን ፡ የራሱን ፡ "የፖለቲካ ፡ ተዋንያን" ፡ እንኳ ፡ እየመለመለ ፥ "የመልቲ ፡ ፓርቲ ፡ ዴሞክራሲ" ፡ የተሠኘ ፡ የሚያፈዝ ፡ የሚያደነግዝ ፡ ያሻንጉሊት ፡ ተውኔቱን ፡ በድጐማው ፡ አስፋፍቶ ፡ ማሳየቱን ፡ ቀጠለ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ችግሮች ፡ እየተባባሱ ፥ መፍትሔ ፡ ወደሚያጡበት ፡ የምናውቀው ፡ አረንቋ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ተዘፈቁ ።

ጠላት ፡ በነሲብ ፡ አይሠራም ። ጠቅላላ ፡ የጠላትነት ፡ ዘመቻውን ፥ ዐቅድ ፡ አውጥቶለት ፥ ረድፍ ፡ በረድፍ ፡ ይመራዋል ። ትላንት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አንድነትና ፡ ነጻነት ፡ የሚታገል ፡ "ገጸ ፡ ባሕርይ"ን ፡ ያሳዩ ፡ የነበሩ ፡ አሻንጉሊት-ተዋንያን ፥ ዛሬ ፡ ለ"ዐማራዊ" ፡ ነጻነት ፡ በሚታገሉ ፡ ትውልደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አሻንጉሊት-ተዋንያን ፡ ተተክተዋል ። ትላንት ፡ "ለዜግነት ፡ ፖለቲካ" ፡ የሚታገል ፡ "ገጸ ፡ ባሕርይ"ን ፡ ያሳዩ ፡ የነበሩ ፡ አሻንጉሊት-ተዋንያን ፥ ዛሬ ፥ ቃል ፡ በቃል ፥ "ላማራ ፡ የማትኾን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባፍንጫዬ ፡ ትውጣ" ፡ በሚሉ ፡ ኢትዮጵያዊነታቸውን ፡ በለወጡ ፡ ትውልደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አሻንጉሊት-ተዋንያን ፡ ተተክተዋል ። ከእነዚህኞቹ ፡ ውስጥ ፡ አብዛኞዎቹ ፡ የዋሃን ፡ ወጣቶች ፡ ናቸው ፤ የሕፃናት ፣ የሴቶች ፣ የንጹሓን ፡ መታረድና ፡ መገደል ፡ ኹላችንን ፡ እንዳስቈጣ ፡ እነሱንም ፡ አስቈጥተዋቸዋል ፤ የዓለም ፡ ማወራኛዎች ፡ ዝምታና ፡ ተባባሪነትም ፡ አቃጥለዋቸዋል ፤ እንደዚሁ ፡ ኹሉ ፥ የሌላው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ "ባለሥልጣን-ተብዬ" ፡ ዐድር-ባይነትና ፡ "በልቼ ፡ ልሙት"-እነት ፡ አንገብግበዋቸዋል ። የኾነው ፡ ኾኖ ፥ ክፋት ፡ ሲደረደር ፣ ሲከመር ፣ ሲደማመር ፡ ቢውል ፥ የደንዳናውን ፡ ሕዝብ ፡ እምነትና ፡ አስተሳሰብ ፡ ቢፈታተናቸው ፡ እንጂ ፥ ያናጋቸዋል ፡ ተብሎ ፡ አይታሰብም ። ነገር ፡ ግን ፥ ታሪካውያን ፡ ጠላቶቻችን ፥ ትላንት ፡ ግራ ፡ በተጋባው ፡ የማርክሲዝም-ሌኒኒዝም ፡ አስተሳሰብ ፡ ወጣቱን ፡ ትውልድ ፡ አደናግረው ፡ ባጪር ፡ እንደ ፡ ቀጪ ፡ ኹሉ ፥ ዛሬም ፡ በጠባብና ፡ ጽንፈኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ ወጣቱን ፡ የኅብረተሰብ ፡ ክፍል ፡ ሚዛን ፡ ከመንሣትና ፡ ዳግም ፡ ዘርጥጦ ፡ ከመጣል ፡ እንደማይመለሱ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። ጕዳዩ ፡ ችላ ፡ ሊባል ፡ አይገባውም ።


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

እዚህ ፡ ላይ ፥ በተለይ ፡ "ዐማራዊ" ፡ ለሚለው ፡ "ገጸ ፡ ባሕርይ" ፡ ተገቢው ፡ መተርኰሻ ፡ ቢጤ ፡ ያሻዋል ። **ዐማራ ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የግብር ፡ ስም ፡ መኾኑን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ጠንቅቆ ፡ ያውቀዋል ።** ይህን ፡ የሚክደውን ፡ "ገጸ ፡ ባሕርይ" ፡ የፈጠረብንና ፡ በተውኔት ፡ የሚያንበለብልብን ፡ የምልክዮሽ ፡ (የ imperialism) ፡ ድርሰት ፡ መኾኑን ፡ ሳንዘነጋ ፥ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ዋጋም ፡ ሳንሰጠውና ፡ ሳናራግበው ፥ በጥቂቱ ፡ እንተቸው ።

መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በመኾኑ ፥ የመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባለቤት ፡ የኾነው ፡ ዐማራ ፥ የትም ፡ ቢሰፍር ፥ የሀገሩን ፡ ነጻነት ፣ ዳር ፡ ድንበርና ፡ ሀብት ፡ በቀናተኛነት ፡ ስለሚከላከል ፥ ብዙ ፡ ደመኛ ፡ አለበት ። የምልክዮሽ ፡ ዐይን ፡ ያረፈባቸው ፡ የወርቅ ፡ የአልማዝ ፡ ማዕድናት ፣ የዘይት ፡ የጋዝ ፡ ክምችቶች ፣ ሰፋፊ ፡ የዕርሻና ፡ የዕፀዋት ፡ ሀብቶች ፣ ታላላቅ ፡ የውሃ ፡ ዥረቶች ፡ መገኛ ፡ አካባቢዎች ፡ ኹሉ ፡ በዐማራ ፡ እንቢተኛነት ፡ ታጥረዋል ። ዐማራ ፡ « አላስነካም ! » ፡ ብሏል ።

ታዲያ ፥ ምልክዮሽ ፡ « ዐማራን ፡ አጠፋዋለኹ ! » ፡ ሲል ፥ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊነትን ፡ (ኢትዮጵያዊ ፡ citizenship ን) ፡ አጠፋለኹ ፡ ማለቱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ምልክዮሽ ፡ ራሱ ፡ የፈጠረልን ፡ "አማራዊ"ው ፡ "ገጸ ፡ ባሕርይ" ፡ ይህን ፡ የዐማራን ፡ ትኽክለኛ ፡ ማንነት ፡ አስቀድሞ ፡ ሊክድና ፡ ሊያሳስት ፡ ቆሟል ። ትኽክለኛውን ፡ የዐማራን ፡ ማንነት ፡ እንዲህ ፡ ገልጦ ፡ የሚነግረውን ፡ ኹሉ ፥ ይህ ፡ "ገጸ ፡ ባሕርይ" ፦ « ድንቄም ! » ፡ ብሎ ፡ ይገረምመዋል ፤ ከዚያም ፦ « ኢትዮጵያ ! ኢትዮጵያ ! ማለት ፡ ለዐማራ ፡ ከሞት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አላመጣለት ! » እያለ ፡ ሊያሳጣም ፡ ይሞክራል ። ጠላት ፥ ላለፉት ፡ 50 ፡ ዓመታት ፦ « ዐማራ ፥ ከ 84 ቱ ፡ "ብሔር ፣ ብሔረሰቦችና ፡ ሕዝቦች" ፡ አንዱ ፡ ነው » ፡ የሚልበትን ፡ ንኀለተኛ ፡ (nihilist) ፡ ስብከቱን ፡ ሳያቋርጥ ፡ በመንዛቱ ፥ ትንሽም ፡ ቢኾን ፥ ባስተሳሰቡ ፡ የተፈናቀለ ፡ ወጣት ፡ የኅብረተሰብ ፡ ክፍልን ፡ አፍርቷል ። በዚህ ፡ የተሳሳተ ፡ አስተሳሰብ ፡ መሠረት ፦ « "ዐማራ" ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ ነው ፤ በማንነቱ ፡ ተጠቅቷል ፤ ስለዚህ ፡ የራሱን ፡ ህልውና ፡ የሚያስከብርበትን ፡ ግዛቱን ፡ በመገንጠል ፡ ያቋቁም ! » ፡ ወደሚል ፡ የጥፋት ፡ አዝማሚያ ፡ ያማልሉታል ።

« ገንፎ ፥ እፍ ! እፍ ! ቢሉሽ ፥ ሊውጡሽ » ፥ በሀገራዊነታቸው ፡ ኢትዮጵያውያን / ዐማራዎች ፡ ኾነው ፥ በውልደት ፡ ግን ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ውልደቶች ፡ የሚወለዱትን ፡ ደግሞ ፦ « ካልተገነጠላችኹ ፡ በቀር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ በሰላምና ፡ በነጻነት ፡ መኖር ፡ ከቶ ፡ አይቻላችኹምና ፥ አንድ ፡ ፊቱን ፡ ተገንጠሉ ! ሌሎች ፡ ሀገሮች ፡ እንደኖሩት ፡ "ኦሮሚያ"ም ፣ "ትግራይ"ም ፣ "አጋዴኒያ"ም ፣ ወዘተርፈ ፡ ... ፡ መኖር ፡ አያቅታቸውም ! » ፡ እያሉ ፡ ያስጐመዧቸዋል ፤ ለዚህም ፡ የንጹሓንን ፡ ደም ፡ እንዲያፈሱና ፡ ደም ፡ እንዲቃቡ ፡ ያነሣሧቸዋል ። አቤት ፡ ግፍ ! የንጹሓን ፡ መታረድ ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፥ አስሠቃቂ ፡ ሞታቸው ፡ ለተጨማሪ ፡ ጥፋት ፡ መጥሪያ ፡ ይዋል ?! ይህን ፡ የመሰለውን ፡ የግፍ ፡ ግፍ ፡ ከምልክዮሽ ፡ ሌላ ፡ ማንም ፡ አያስበው ፣ አይደፍረውም ። ተውኔቱም ፥ በዠርባው ፡ የዘመቻውን ፡ ጠቅላላ ፡ ዐቅድ ፡ ዐዝሏል ፤ ርሱም ፦ « ኢትዮጵያን ፡ የሠራውንና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባለቤት ፡ የኾነውን ፡ የዐማራን ፡ ወይም ፡ የመላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ አንድነትና ፡ ህልውና ፡ በመካድ ፥ ዐማራን ፡ እጎሳ ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ አድርጎና ፡ በጠባብ ፡ ክልል ፡ ቀንብቦ ፥ አንዱን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብም ፡ "ሕዝቦች" ፡ አስሠኝቶ ፡ በታትኖ ፥ ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባለቤት ፡ ማሳጣትና ፥ መጨረሻውን ፥ ኢትዮጵያን ፡ ከፋፍሎ ፡ መቀራመት ! » ፡ የሚል ፡ ነው ።

የእነዚህ ፡ የ"ፖለቲካ" ፡ ተውኔቶች ፡ ግብ ፥ የሕዝብን ፡ ናላ ፡ ፈጽሞ ፡ ማጦዝና ፥ ለተፈለገው ፡ የከፋፍለኽ ፡ ግዛ ፡ የጎሳ ፡ "ፖለቲካ" ፡ ውዝግብ ፡ አሰናድቶ ፥ ለማይቀረው ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ፍጅትና ፡ ለሀገር ፡ ውድመት ፡ መዳረግ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ረገድ ፥ ታሪካውያን ፡ ጠላቶቻችንን ፡ ለጊዜው ፡ ቀንቷቸዋል ፡ ማለት ፡ ይቻላል ፤ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ የሚያመጡትን ፡ መዐት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወቅ ፡ እንጂ ፥ በኢትዮጵያስ ፡ ላይ ፡ የጥፋት ፡ ዐቅዳቸውን ፡ በትጋትና ፡ በፍጹም ፡ ጭካኔ ፡ መፈጸማቸውን ፡ ቀጥለዋል ። « ተዉ ! ይቅርባችኹ ! » ፡ በተባሉ ፡ ቍጥር ፡ እንዲያውም ― የባሰውን ፡ እልክ ፡ እየያዛቸው ― ወደከፋው ፡ ጭካኔ ፡ በጽንት ፡ የሚንደረደሩ ፡ እንጂ ፦ « ቈይ ፡ እስቲ ፡ ... » ፡ ብለው ፡ ትንሽ ፡ እንኳ ፡ ገንግነው ፡ የሚገቱ ፡ አልኾኑም ።

« እነሱስ ፡ እሺ ፤ ታዲያ ፡ ... ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ምን ፡ ነካው ፧ ያን ፡ ኀያል ፡ ሕዝብ ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ አገኘው ፧ » ብለው ፡ የሚገረሙ ፡ አሉ ።

ለወትሮው ፡ የዝንብ ፡ ጠንጋራን ፡ የሚለየው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ አኹንም ፡ ደባ ፡ እንደሚፈጸምበት ፡ አላጣውም ። በሚቀርቡለት ፡ የ"ፖለቲካ" ፡ ተውኔቶች ፡ ራሱን ፡ ማየቱ ፡ ከቀረ ፡ ዘመናት ፡ ዐልፈዋል ። ነገር ፡ ግን ፥ ፊዞ ፡ መመልከቱን ፡ አልተወም ፤ ኀይሉን ፡ አስተባብሮ ፥ ሀገራዊ ፡ ችግሩን ፡ ባንድነት ፡ መፍታት ፡ ለጊዜው ፡ የተሳነው ፡ ይመስላል ። በረዥሙ ፡ የሀገርነት ፡ ታሪኩ ፥ ይህ ፡ ዐዲስ ፡ ኹኔታ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ በ 20 ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ካገኛት ፡ ስብራት ፡ ገና ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

አለማገገሟን ፡ ያረጋግጥልናል ።  ቀድሞ ፡ የነበሯት ፡ ትውፊታውያን ፡ የማኅበርና ፡ የግዛት ፡ አወቃቀሮች ፥ በዘመናዊነት ፡ ስም ፡ እንዲሁም ፡ በ"ሥር-ነቀል" ፡ አብዮታዊ ፡ ዐመፅ ፡ "ኋላ-ቀር" ፡ ተብለው ፡ ከመሠረታቸው ፡ ሲፈነቀሉ ፥  የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ የሥልጣን ፡ ተዋረድን ፡ ጠብቆ ፥  በአንድነት ፡ የሚነሣባቸውና ፡ የሚስሰማራባቸው ፡ ትውፊታውያን ፡ ሥርዐቶቹ ፡ ዐብረው ፡ ስለተደመሰሱበት ፥  ዱሮ ፡ የማይታዩበት ፡ መደናገር ፣  መተሻሸትና ፡ ማመንታት ፡ ዛሬ ፡ አግኝተውታል ።

ሕዝብን ፡ አንድ*ጋ ፡ የሚያስነሣና ፡ የሚያስሰማራ ፡ ይህ ፡ ሀገራዊና ፡ ማኅበራዊ ፡ የሥልጣን ፡ መዋቅር ፡ ዳግመኛ ፡ ዘምኖ ፡ እስኪጸና ፡ ድረስ ፥  አንዳንድ ፡ በንጥላት ፡ የሚታገሉ ፡ እና ፡ የሕይወት ፡ ዋጋን ፡ የሚከፍሉ ፡ እውነተኞች ፡ ዐርበኞች ፡ በውስጥም ፡ በውጭም ፡ ተነሥተዋል ፤  **ፋኖነት ፡ እና ፡ ማኅበራዊ ፡ አንቂነት** ፡ የዚህ ፡ አዝማሚያ ፡ ማሳያዎች ፡ ናቸው ።  እነሱም ፡ ቢኾኑ ፥  በእየጊዜው ፥  በወረንጦ ፡ እየተለቀሙ ፡ በእስርና ፡ በዐፈና ፣  በስደትና ፡ በግድያ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ አላንዳች ፡ ምሕረት ፡ ይወገዳሉ ፤  የተረፉት ፥  በማያባራ ፡ ብቀታና ፡ ፍትራ ፡ ሲጕላሉ ፣  በረኃብና ፡ በችጋር ፡ ዐለንጋ ፡ ሲገረፉ ፡ ይኖራሉ ።  ደግነቱ ፥  ይህን ፡ የመሰለው ፡ ጥቃት ፡ ኹሉ ፥  የሀገራውያኑን ፡ ሚና ፡ እየኰተኰተውና ፡ ይበልጡን ፡ እያለመለመው ፡ ስለ ፡ ኼደ ፥  ሕዝባዊው ፡ የለውጥ ፡ ማዕበል ፡ ከንግዲህ ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ ተቀስቅሶ ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሊያዳርስ ፡ እንደሚችል ፡ ምልክቶች ፡ ኹሉ ፡ ቀድመው ፡ አረጋግጠውልናል ።

ሀገራዊ ፡ ለውጥ ፡ በዕቅድ ፡ አይመጣም ፣  አይመራምም ፤  ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ድንገት ፡ እንደ ፡ ጀንበር ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ይከሠታል ።  የተለመደው ፥  *« ሰርገኛ ፡ መጣ ፤  በርበሬ ፡ ቀንጥሱ »* ፡ እንዳያገኘን ፥  ለውጡ ፡ ድንገት ፡ ከመከሠቱ ፡ በፊት ፥  ለደገኛ ፡ ግሥጋሤውና ፡ ሰላማዊ ፡ አፈጻጸሙ ፡ ካኹኑ ፡ ተፈላጊው ፡ የመሸጋገሪያ ፡ ዝግጅት ፡ ሊጠናቀቅለት ፡ ይገባል ።

በታሪካውያን ፡ ጠላቶቹ ፡ ተቀናብሮ ፡ በ"**መልቲ ፡ ፓርቲ ፡ ዲሞክራሲ**" ፡ ስም ፡ ሲቀርብለት ፡ የኖረውን ፡ ያሻንጕሊት ፡ ተውኔት ፡ ከእንግዲህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መመልከቱን ፡ ርግፍ ፡ አድርጎ ፡ መተው ፡ ይኖርበታል ።  የ"ፖለቲካ ፡ ፓርቲዎች" ፡ ዕጣ ፡ ፈንታ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ባዲሱ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ የሚወስነው ፡ ጕዳይ ፡ እንጂ ፥  *እምነበ ፡ አልቦ* ፡ በሀገር ፡ ላይ ፡ የሚቈለል ፡ ዕዳ ፡ አይኾንም ።

በሙስና ፡ ከተደወየውም ፡ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ቅሬታ ፡ ይዘትና ፡ ከሸንበቆ ፡ ምርኵዙ ፡ "ሻዕቢያ" ፥  ፍርሰትን ፡ እንጂ ፡ ድኅነትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አይጠብቅ ።  እጫንቃው ፡ ላይ ፡ የተንዘራፈጡበትን ፡ በጣት ፡ የሚቈጠሩ ፡ መንደር-ገነኖች ፡ አሽቀንጥሮ ፡ ጥሎ ፥  ከአብራኩ ፡ የወጡትን ፣  በእሳት ፡ ተፈትነው ፣  ወርቅ ፡ ኾነው ፡ የተገኙትን ፣  የሚታመኑትን ፡ የትግል ፡ መሪዎቹን ፡ ራሱ ፡ በቀጥታ ፡ መርጦ ፡ ይሹም ! ከቀበሌ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ወረዳ ፣  አውራጃ ፣  ክፍለ ፡ ሀገርና ፡ ሀገር ፡ ደረጃ ፥  በእየዕርከኑ ፡ ለሚሠይማቸው ፡ የጐበዝ ፡ አለቆቹ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፥  ለማንም ፡ መንደር-ገነን ፡ ላይገዛ ፡ ምሎ ፡ መነሣት ፡ አለበት ።  የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በዚህ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንገድ ፡ የአንድነት ፡ ሥልጣኑን ፡ የሚያሳርግበትንና ፡ ትግሉን ፡ አስተባብሮ ፡ የሚመራበትን ፡ ሥርዐቱን ፡ ሲያበጅ ፥  ይህ ፡ የመደነጋገር ፡ ያጨቢር ፡ ጊዜ ፡ አሳዛኝ ፡ ታሪኩ ፡ ያከትማል ፤  ለውጡም ፥  በተደራጁ ፡ የጥፋት ፡ ቡድኖች ፡ ሳይጠለፍበት ፥  በሰላም ፡ ይጠናቀቃል ።  የጋራ ፡ ፈቃዱን ፡ ሕግ ፡ እያደረገ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ሲገዛም ፥  የጥንት ፡ ታላቅነቱ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ይመለስለታል ፤  ሀገሩ ፡ ኢትዮጵያም ፥  እግዚአናዋ ፡ በዓለም ፡ ተከብሮ ፥  ርትዓዊ ፡ የሥልጣኔ ፡ ጕዞዋን ፡ በሰላም ፡ ትቀጥላለች ።

**ኢ.ህ.ሥ.አ.** ፥  መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ፡ ያጸደቀውና ፥  በቅርቡ ፡ ይፋ ፡ የሚያወጣው ፦

***« ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ሀገራዊ ፡ ቅያስ »*** ፡

ይህን ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ ሥምረት ፡ ለማስገኘትና ፡ ሰላማዊ ፡ ሽግግሩን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የተሰናዳ ፡ ሀገራዊ ፡ ዐቅድ ፡ ነውና ፥  መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አጥንቶት ፣  መክሮበትና ፡ ዘክሮበት ፡ ሲስማማበት ፥  ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ በአንድነት ፡ በመነሣትና ፡ በርሱ ፡ አማካይነት ፡ በመመራት ፥  ሀገሩን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ዳግመኛ ፡ ይታደግበታል ❖

እግዚአናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕግ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ህ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ፡፡
www.slttunhzb.net


©ኢ.ህ.ሥ.አ. ፥  2015 ፡ ዓ.ም. ።